ምድብ አምስት (ከ10ኛ — 12ኛ) ክፍል

29 ኛ ሳምንት

# የክብር ትንሣኤ (I)

## የትምህርቱ ዓላማ

- ይህ ክፍለ ትምህርት በሁለት ተከታታይ ክፍል ከትንሣኤ በኋላ ስላለው የክርስቶስ ክቡር አካል የምንማረው የመጀመሪያ ክፍል ነው፡፡
- እንደ ክርስቶስ የክብር ትንሣኤ እንደምንነሳ የክርስትና ትምህርታችን መሠረታዊ ትምህርትና የጌታችን ተስፋ ተሰጥቶናል፡፡
- ስለዚህ የትምህርቱ ዓላማ ስለክርስቶስ ትንሣኤና ስለተስፋችን መማር ነው፡፡

## የሚጠና ጥቅስ

- ***"የሙታን ትንሣኤ ደግሞ እንዲሁ ነው፡፡በመበስበስ ይዘራል÷ባለመበስበስ ይነሣል፤ በውርደት ይዘራል÷ በክርብር ይነሣል፡፡"*** 2ኛ ቆሮ. 15÷42

## የሚተኮርባቸው ነጥቦች

<u>**ሀ.ጥያቄ**</u> ጌታ ሲነሣ ምን ዓይነት አካል ይዞ ተነሣ? እንደ እኛ ተራ አካል ይዞ ነው የተነሣው ወይስ የክብር አካል? ክቡር አካል ይዞ ከተነሣ ***"ተቀብሎም በፊታቸው በላ"*** ሉቃ 24÷43 ***"እኔን ዳሳስችሁ እዮ አላቸው፡፡ ይህንም ብሎ እጆቹንና እግሮቹን አሳያቸው፡፡"*** ሉቃ.24÷39 የሚሉት ቃላት ትርጓሜ ምንድን ነው? ክርስቶስ ሲነሣ የነበረው አካል ከድንግል ማርያም ከነሣው አካል ጋር አንድ ነው? በክብር አካል ተወለደስ ለምን አንልም?

<u>**ለ. መልስ**</u> (1) ካለ ጥርጥር የተነሣው ክቡር አካል ነው፡፡

- ቅዱስ ጳውሎስ ስለዚህ የክብር አካል ሲገልፅ እንዲህ ብሏል፡፡ ***"የሙታን ትንሣኤ ደግሞ እንዲሁ ነው፡፡በመበስበስ ይዘራል÷ባለመበስበስ ይነሣል፤ በውርደት ይዘራል÷ በክርብር ይነሣል፡፡በድካም ይዘራል÷ በኃይል ይነሣል፤ ፍጥረታዊ አካል ይዘራል÷ መንፈሳዊ አካል ይነሣል፡፡ ፍጥረታዊ አካል ካለ መንፈሳዊ አካል ደግሞ አለ፡፡"1ኛ*** ቆሮ.15÷42-44

(2) እኛ በክብር አካል የምንነሣ ከሆነ÷የክርስቶስ ትንሣኤ ምን ያህል ይልቃል? እኛ የእርሱን ትንሣኤ መስለን በክብር ስለምንነሣበት ግልጥ ትምህርትን የጻፈልን ቅዱስ ጳውሎስ በፊልጵስዮስ መልእክቱ 3÷21 ላይ እንዲህ ጽፎአል፡፡***"ክቡር ሥጋውን እንዲመስል የተዋረደውን ሥጋችንን ይለውጣል፡፡"***

(3) ታዲያ ይህ ከሆነ ክርስቶስ ከተነሣ በኋላ "በላ" "አጥንትና ሥጋ" አለው፡፡ ***"ዳስሱ"*** ለምን ተባለ? ቅዱስ ሉቃስ በጻፈልን የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት መሠረት ይህ ሓሳብ እጅግ ግልጥ ሆኖ ቀርቧል፡፡

- ወንጌላዊው ጌታችን ከትንሣኤው በኋላ ራሱን ለደቀመዛሙርቱ መግለጡን ሲጽፍ ***"ነገር ግን ደነገጡና ፈሩ መንፈስም ያዩ መሰላቸው፡፡ እርሱም፡- ስለምን ትደነግጣላችሁ? ስለ ምንስ አሳብ በልባችሁ ይነሣል? እኔ ራሴ እንደሆንሁ እጆቼንና እግሮቼን እዩ በእኔ እንደምታዩት መንፈስ ሥጋና አጥንት የለውምና እኔን ዳስሳችሁ እዩ አላቸው፡፡ ይህንም ብሎ እጆቹንና እግሮቹን አሳያቸው፡፡"*** ሉቃ. 24÷37-40 በተመሳሳይ ቦታና ጊዜም ***"የተጠበሰ ዓሣ ከማር ወለላ ጋር በፊታቸው በልቷል፡፡"*** ሉቃ. 24÷42-43
- ይሄንንስ እንዴት እንገልጸዋለን?

1.ስለመንፈሳዊው አካል ምንነትና ክብር አላወቁም ነበርና÷ሥጋው ከሙታን መነሣቱን ሊያረጋግጥላቸው……..
በርግጥም በመብላትና አካሉን እንዲዳስሱ በማድረግ ባያረጋግጥላቸው ኖሮ ሥጋ የሌለው መንፈስ ያዩ መስሏቸዋልና ትንሣኤውን ይጠራጠሩ ነበር፡፡

2.**በትንሣኤ በጣም አስፈላጊው ነገር *የሥጋ መነሣት* ነው፡፡ከላይ እንደተገለጸው ደቀመዛሙርቱ መንፈስ ያዩ የመሠላቸው የሥጋ ትንሣኤ ከአዕምሮአቸው እጅግ የራቀ ሐሳብ ስለነበር ነው፡፡**

❖*ምክንያቱም መንፈስ በተፈጥሮው የማይሞት ሕያው ነው፡፡ሥጋ የሚሞተውም ከመንፈስ ሲለይ ነው÷ከዚያም ወደ አፈርነት ይቀያራል÷ነገር ግን መንፈስ በመቆያ ሥፍራው (ገነት ወይም ሲኦል) ይቆያል፡፡እንግዲህ ትንሣኤ የሥጋ መነሣትና ከመንፈስ/ነፍስ/ ጋር መዋሀድ ነው፡፡*

❖ስለዚህም ከዚህ እምነት የራቀ አዕምሮአቸውን ለማሣመንና ሌሎቹንም እንዲያሳምኑ ለማድረግ መብላትናአካሉን ማስዳሰስ

አስፈልጎል፡፡

❖*መንፈስ ብቻውን ሙሉ የሰውን ተፈጥሮ አይወክልም፡፡ለዚህም ነው የሥጋን ትንሣኤ ማስረገጥ ያስፈለገው፡፡ደቀመዛሙርቱን*

*ዳስሳችሁ እዩ ብሎ የፈቀደላቸው ለዚህ ነው፡፡* (ሉቃ 24÷39 ዮሐ. 20÷27)

3. **ይህ *መንፈሳዊ* ክቡር አካል ነው ወደ ሰማይ የወጣው፡፡*ሥጋ*** ከአየር የሚበልጥ ክብደት ስላለው ነገረ ዕረገት ከመሬት የስበት ኃይል ሕግ ጋር ላይስማማ ይችላል፡፡ነገር ግን በክብር ከመንፈሳዊው አካል ጋር ወደ ሰማይ ዐርጎል፡፡በተመሳሳይ ክብርም በአብ ቀኝ ተቀምጦል፡፡ተመሳሳይ የክብር አካልም ይመጣል፡፡/ማቴ. 25÷37/

4.**ይህ የክብር አካል ነው ለሳውል በጠርሴስ መንገድ ላይ የተገለጠለት**(የሐዋ.9÷3-5)

5.**ይህ የክብር አካል ነው ከድንግል ማርያም ከተወለደው ጋር አንድ ነው፡፡**

❖ ሲወለድ የነሣው *ሥጋ* በትንሣኤ እንደ ነበረው የከበረ አይደለም ምክንያቱም ሲወለድ ***"የባርያን መልክ ይዞ በሰውም ምሳሌ ሆኖ ራሱን ባዶ አደረገ*** "ፊልጵ.2÷7 ራሱን ባዶ ማድረጉም በክቡር ትንሣኤውና እርገቱ ተፈጽሞል፡፡

6.**የተነሳው *ሥጋ* ከተወለደው ጋር አንድ ነው፤ሲለወጥ**…ምን እንደሚመስል ግን በደብረ ታቦር ምሳሌ ሠጥቶናል ነው፡፡

❖ ***"ወደረጅም ተራራ ብቻቸውን አወጣቸው፡፡ በፊታቸውም ተለወጠ÷"*** ማር.9÷2-3

❖ ክርስቶስ በትንሣኤ የነበረው *ሥጋ* ሲወለድ ከነበረው *ሥጋ* ጋር አንድ ነው፡፡በክብር እና በመለወጥ ግን *ሥጋ*ውን በክቡር ባሕርይው እና በመንፈሳዊ ኃይሉ ገልጦታል፡፡ይህ ተመሳሳይ ነገርም በእኛ ይሆናል፡፡

7.አንዳንዶች የክርስቶስ አካል የክብር ባሕርይውን የወሰደው ከትንሣኤው ወይም ከዕርገቱ በኂላ ነው? ብለው ይጠይቃሉ? መልሳችን የክርስቶስ አካል ያን ባሕርይ የተላበሠው በትንሣኤው ነው ሰውኛ ባሕርይውን ለማረጋገጥ ያደረጋቸው ልዩ ምክንያቶችም ለደቀመዛሙርቱ *ሥጋ*ው መነሣቱን ለማሣመንና በሙሉ ልብ ወንጌልን እንዲያስፋፉ ነበር፡፡/1ኛ ዮሐ.1÷1 የሐዋ.*ሥ*.10÷41)

❖ ከዚህምክንያትውጪግንየተነሣውየክብርአካልመብልናመጠጥአያስፈልገውም፡፡አይራብም÷አይጠማም፡፡በክብርአካልድካምየለም፡፡አይታመምም፡፡አይሞትምም፡፡ሕያው፣መንፈሳዊና ክቡር አካል ነውና፡፡

<u>ማጠቃለያ</u>

1. የተለያዩ አካላት አሉ፡፡እጅግ አስፈላጊው አካል ከሞት ስንነሣ ይዘን የምንነሣው የክብር አካል ነው፡፡በምድር የጽድቅ ኑሮ ከኖርን፣ ከጌታችን ጋር አንድ ሆነን (በሥጋና ደሙ) ከኖርን÷በዳግም ምጽአቱ ስናገኘውም ከክርስቶስ ጋር (ከተነሣበት *ሥጋ* ጋር)ተመሣሣይ የሆነ የክብር አካል ይኖረናል፤
2. ትንሣኤ የክርስትና ክብር ነው፡፡ምክንያቱም መጻኢ ሕይወታችንን የደስታ ዘላለማዊ ሕይወትን ከእግዚአብሔር ጋር ያኖረናል፡፡

**ይቆየን፡፡**